የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

$26^{n}$ Year No. 23
ADDIS ABABA 13$^{th}$ March, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፪/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በአፍሪካ ህዝቦች እና ሰዎች መብቶች ቻርተር የአፍሪካ አረጋዊያን ፕሮቶኮል ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………………………………ገጽ ፲፪ሺ፪፻፸፪

**Content**

Proclamation No· 1182/2020

Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa Ratification Proclamation……………………………...Page 12272

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፪/፪ሺ፲፪

## በአፍሪካ ህዝቦች እና ሰዎች መብቶች ቻርተር የአፍሪካ አረጋዊያን መብቶች ፕሮቶኮል ለማጸደቅ የወጣ አዋጅ

የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ስምምነት የአፍሪካ የአፍሪካ አረጋዊያን መብቶች ፕሮቶኮል ጥር ፳፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም አዲስ አበባ በተደረገው ፳፮ኛ መደበኛ የመሪዎች ጉባኤ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታወጇል።

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በአፍሪካ ህዝቦች እና ሰዎች መብቶች ቻርተር የአፍሪካ አረጋዊያን ፕሮቶኮል ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር

## PROCLAMATION NO. 1182/2020

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE PROTOCOL TO THE AFRICAN CHARTER ON HUMAN AND PEOPLES' RIGHTS ON THE RIGHTS OF OLDER PERSONS IN AFRICA

**WHEREAS**, the African Union Adopted the Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa during the 26$^{th}$ Ordinary Summit of the Heads of States and Governments held on 31 January 2016 in Addis Ababa;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 13$^{th}$ day of February , 2020;

**NOW, THERERORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa Ratification Proclamation No.1182./2020".



www.chilot.me

፩ሺ፩፻፹፪/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.<u>በስምምነቱ ላይ የገቡ ተዓቅቦዎች እና መግለጫዎች</u>**

፩/የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚከተሉት የፕሮቶኮሉ አንቀጾች ላይ ተአቅቦ አድርጓል፤

ሀ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፕሮቶኮሉ አንቀጽ ፳፪ (፫ እና ፬) ተገገር አይሆንም፡፡

፪/የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚከተሉት የፕሮቶኮሉ አንቀጾች ላይ መግለጫ አስገብቷል፡፡

ሀ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በስምምነቱ የተደነገጉ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን መሟላት አስመልክቶ መንግስት የሚኖርበት ግዴታ የአገሪቱን የኢኮኖሚ አቅም ባገናዘበ መልኩእና በጊዜ ሂደት ተግባራዊ እንደሚሆን ይገልጻል፡፡

**፫. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በአፍሪካ አረጋዊያን መብቶች ፕሮቶኮል ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

**፬.<u>አስፈፃሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአፍሪካ አረጋዊያን ፕሮቶኮልን የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፭.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**2. <u>Reservations and Declarations entered in the Protocol</u>**

1/The Federal Democratic Republic of Ethiopia entered reservations onthe following provisions of the Protocol.

a) The Federal Democratic Republic of Ethiopia does not consider itself bound by the provisions of Article 22(3 and 4)

2/The Federal Democratic Republic of Ethiopia entered declarations on the following provisions of the Protocol.

a) the Federal Democratic Republic of Ethiopia understands the obligation of the Government for the realization of the Social and economic Rights provided under the Protocol subject to the available economic resource of the country and a progressive regime.

**3· <u>Ratification of the Protocol</u>**

Protocol to the African Charter on Human and Peoples' Rights on the Rights of Older Persons in Africa is hereby ratified.

**4· <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Labour and Social Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia in collaboration with other concerned bodies is hereby empowered to implement the Rights of Older Persons Protocol.

**5 ·<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March , 2020·**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

www.chilot.me